Washington State Department of Social & Health Services

JAS ID
CASE NUMBER
CLIENT ID

የግለሰብ ኃላፊነት ዕቅድ (IRP) የሕክምና ማስረጃ ማግኘት

Individual Responsibility Plan (IRP) Obtaining Medical Evidence

የወርክፈርስት የግለሰብ ኃላፊነት ዕቅድ ለ_____

ስለሚከተሉት ይገባኛል፥

- *ሥራ መሥራት፣ ሥራ መፈለግ፣ ወይም ለሥራ መዘጋጀት ይጠበቅብኛል።*
- የሚያስፈልጉ ተግባራትን ማድረግ እንዳለብኝ። ካላደረግሁ፣ ጥሩ ምክንያት እንዳለኝ ማስረዳት ካልቻልኩ መቀጫ እንደሚደረግብኝ። ይህ በወርክፈርስት ዕቀባ ሁኔታ ላይ መዋል ይባላል። ዕቀባ ከተደረገብኝ፣ ይህ ማለት፥
  - እርዳታዬ (ግራንት) በ 40 በመቶ ወይም በአንድ ሰው ድርሻ መጠን ፣ በለጥ ባለው፣ እንደሚቀነስ።
  - ከዕቀባ ለመውጣት የእኔን IRP በተከታታይ ለአራት ሳምንታት መከታተል አለብኝ።
  - አንዴ የሚጠበቀውን በተከታታይ ለአራት ሳምንታት ካደረግሁ፣ የአራት ሳምንታት ተካፋይነቴን አስከትሎ በሚገኘው የመጀመሪያ ወር ጀምሮ የዕቀባ መቀጫዬ እንደሚነሳልኝ።
  - በተከታታይ ለአራት ወራት በዕቀባ ሥር ከቆየሁ ጉዳዬ ሊዘጋ ይችላል።
    - ጉዳዬ ከተዘጋ፣ ገንዘብ ከመቀበሌ በፊት እንደገና ማመልከቻ ማስገባትና በተከታታይ ለአራት ሳምንታት መሳተፍ አለብኝ።
    - ጉዳዬ ሶስት (3) ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከተዘጋ፣ የ TANF/SFA ዕርዳታ እንዳላገኝ እስከመጨረሻው ልታገድ እችላለሁ።
    - ከመጋቢት 1, 2007 አንስቶ በወርክፈርስት ዕቀባ ምክንያት ጉዳዬ _____ ጊዜ ተዘግቶ ነበር።
- የ TANF/SFA እርዳታዎች በማግኘት ላይ እያለሁ ከልጅ ማሳደጊያ ክፍል ጋር ትብብር ማድረግ እንዳለብኝ፣ ትብብር ላለማድረግ ጥሩ ምክንያት ካለኝ በስተቀር። የልጅ ማሳደጊያዬን በስኬታማነት ማስከፈል መቻል የገንዘብ እርዳታን አስፈላጊነት ያስወግዳል።
- እንዲራዘምልኝ ብቁ ከሆንኩ እንጂ፤ በሕይወቴ ሙሉ የ 60 ወራት ብቻ የ TANF/SFA የገንዘብ እርዳታዎች ማግኘት እንደምችል።
- የ _____ ወራት የገንዘብ እርዳታዎችን እንደተጠቀምኩ።
- *ሥራ መሥራት፣ ሥራ መፈለግ፣ ወይም ለሥራ መዘጋጀት ይጠበቅብኛል*። በተመደበው ተግባር ላይ መገኘት ካልቻልኩ፣ ከዚህ በታች በተጠቀሰው ቁጥር ለሚገኙት ሰው እደውላለሁ።
- ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ለእያንዳንዱ ሳምንት ለጠቀሰው የጊዜ መጠን የሚከትሉትን ተግባራት ማድረግ እንዳለብኝ፥

OR – የሕክምና ማስረጃ ማግኘት

በአንዳንድ የወርክፈርስት ተግባራት ወይም ሥራ ላይ ተካፋይ የመሆኛ ችሎታዬን ሊያውኩ የሚችሉ የአካል፣ ያእምሮ፣ ወይም የስሜት ሕመም ሁኔታዎች እንዳሉብኝ አምናለሁ። የእኔን የወርክፈርስት ፕሮግራም ልዩ ባለሙያ(ስፔሺያሊስት) ወይም የሕብረተሰብ ጉዳይ ሠራተኛ (ሶሺያልወርከር) የጤና ጉዳዮቼን እንዲያጠኑና ለልዩ አስፈላጊ ሁኔታዎቼና ውስንነቶቼ የሚስማማ የግለሰብ ኃላፊነት ዕቅድ ለማዘጋጀት እንዲያስችላቸው ከሕክምና ባለሙያ የሚከተለውን የሕክምና ማስረጃ ለማግኘት እስማማለሁ።

1. የተሟላ DSHS 10-353፣ ለአካል መታነል/ለአስቸጋሪ ሁኔታ መጠየቂያ ሰነድ ቅጽ ወይም የሚከተሉትን የሚገልጽ አማራጭ ሰነድ ዓይነት፥
   a. የምርመራ ውጤቶች፣
   b. የጤና ሁኔታዎቼ ለምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ ተብለው እንደሚገመቱ፣
   c. ከጤና ሁኔታዎቼ የሚመጡ ልዩ የሆኑ ውስንነቶች፣
   d. ለጤና ሁኔታዎቼ መፍትሄ ለመፈለግ የተደረጉ ልዩ የሕክምና ዕቅዶች፣ እና
   e. በእያንዳንዱ ሳምንት ሥራ መሥራት፣ ሥራ መፈለግ ወይም ለሥራ መዘጋጀት የምችልባቸውን የሰዓቶች ብዛት።
2. ለወቅታዊ የሕክምና ሁኔታዬ ዝርዝር መግለጫ ሰንጠረዥ (ቻርትኖት)፣ ሁኔታዬ ለ 3 ወራት ወይም ላነሰ ጊዜ እንደሚቆይ ከታሰበ በስተቀር።

DSHS ለሕክምና መረጃዎች እንዳስፈላጊነቱ እንደሚከፍል ይገባኛል። ይህን የሕክምና ማስረጃ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት የወርክፈርስት ልዩ ባለሙያ (ስፔሺያሊስት) ወይም የሕብረተሰብ ጉዳይ ሠራተኛ (ሶሺያልወርከር) እስከ _____ድረስ ባለው ጊዜ መልሼ ለመስጠት እስማማለሁ።

ዕቅዴን ላለመከተል ጥሩ ምክንያት ካለ፣ በተቻለ መጠን በቶሎ ደውዬ ከወርክፈርስት ፕሮግራም ስፔሺያሊስት/የሕብረተሰብ ጉዳይ ሠራተኛ ጋር መተባበር አለብኝ። የጥሩ ምክንያቶች ጥቂት ምሳሌዎችን የሚያጠቃልሉት፥

- በሕመም ወይም ያልተጠበቀ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ወይም መጓጓዣ መቋረጥ ምክንያት ቀጠሮ ካመለጠኝ፤
- የድንገተኛ ሁኔታ ካለብኝ (የአካል፣ የአእምሮ፣ ወይም የስሜት)፤
- የቤተሰብ ብጥብጥ ተጠቂ ከሆንኩ፤
- ዕድሜያቸው ከ 13 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች በአካባቢዬ የገን፣ ተገቢ የሆነ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት ማግኘት ካልቻልኩ፤
- አስቸኳይ ሕግ-ነክ ችግር ካለበኝ፤
- የአካል መታነል ወይም የተወሰኑ ሁኔታዎች ካሉብኝና ይህ ሁኔታ የፕሮግራሙን መመዘኛ ነጥቦች ማሟላት እንዳልችል ካገደኝ፤ ወይም
- ጽኑና የቆየ አካል መታነል ያለብኝ ነልማሳ ነኝ፤
- ልዩ እንክብካቤ ለሚያስፈልገው ልጅ ወይም በአካል ለታነሉ ሌላ ነልማሳ ሰው እንክብካቤ ለማቅረብ በቤት መገኘት አለብኝ፤
- ዕድሜ 55 ዓመት ወይም ከዚያ በላይና ከሆነና ልጄ ላልሆነ ልጅ ወይም አካለስንኩል ለሆነ ግለሰብ እንክብካቤ የማቀርብ ከሆነ፤ ወይም
- ለ DSHS አስተናባሪ በኩል ለ SSI ማመልከቻ እያስገባሁ ነው።

በዚህ ዕቅድ ካልተስማማሁ፣ ጉዳዩ እንዲጠና እና/ወይም የይግባኝ መብት አለኝ። ይግባኝ ለመጠየቅ፣ የህብረተሰብ አገልግሎት ጽ/ቤትን ማግኘት አለብኝ ወይም በሚከተልው አድራዛ መጻፍ አለብኝ the Office of Administrative Hearings, DSHS, PO Box 42488, Olympia WA 98504-2488 መጠየቅ አለብኝ። የግለሰብ ኃላፊነት ዕቅዴ ቅጅ ተሰጥቶኛል።

CASE MANAGER'S SIGNATURE	DATE	ፊርማዬ	ቀን

ጀኤኤስ መታወቂያ	የጉዳይ ቁጥር	የባለጉዳይ መታወቂያ

በሚስጥር የማስቀመጫ ነጥቦች

በሥራዬ ለማደግ፣ ሥራዬን ይዤ ለመቆየት፣ ሥራ ለመቀበል፣ ሥራ ለመፈለግ፣ ወይም ዕቅዴን ለመከታተል እንዲረዳኝ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማግኘት እችል ይሆናል። በድጋፍ አገልግሎቶች ውሳኔ ካልተስማማሁ፣ ጉዳዩ እንዲጠና እና/ወይም ይግባኝ ልጠይቅ እችላለሁ። የሚከተሉት ዓይነት የድጋፍ አገልግሎቶች ካስፈለጉኝ የወርክፈርስት ፕሮግራም ስፔሺያሊስት/የሕብረተሰብ ጉዳይ ሠራተኛዬን እጠይቃለሁ፥

- መኪና ጥገና
- ልብስ
- ምክር
- ዳይፐር
- የትምህርት ወጪዎች
- የግል ጤና ጥበቃ
- ፈቃድ(ላይሰንስ)/ክፍያዎች
- ፀጉር ለመቆረጥ
- የአውቶቡስ መሣፈሪያ ትኬት
- ማይሌጅ
- ለሥራ መርጃ መሣሪያዎች
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት

በዕቀባ ላይ እያለሁ፣ IRPዬን መከተል እስከምጀምር ድረስ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማግኘት አልችልም (ለሥራ ልብስ ወይም መጓጓዥ ገንዘብ የመሰሉትን)።

ጥሩ ምክንያት ሳይኖር፣ ከልጅ ማሳደጊያ ክፍል (DCS) ጋር ለመተባበር ካልፈቀድኩ፣ እርዳታዬ (ግራንት) እንደሚቀነስ ይገባኛል። ጥሩ ምክንያቶች፣ በልጆቼ ወይም በእኔ ላይ የአካል ጉዳት ሊኖር መቻልን ያጠቃልላሉ። የ TANF እርዳታ በማግኘት ላይ እያለሁ፣ የተሰበሰበ ማንኛውም የልጅ ማሳደጊያ ክፍያ ለስቴቱ መልሶ ለመክፈል ተቀማጭ እንደሚሆን ይገባኛል።

TANF/SFA ማግኘቴን ሳቆም DCS የልጅ ማሳደጊያ ይሰበስብና ይልክልኛል፣ እንዲያቆም ከጠየቅሁ በስተቀር። የድጋፍ አገልግሎቶች፣ ዕቀባዎች፣ እና የልጅ ማሳደጊያ ይገቡኛል።

CASE MANAGER'S SIGNATURE	DATE	ፊርማዬ	ቀን